| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ናደለ፣ | ነከተ፡ | ነቀሰ፡ | ሥልሳ፡ | ዐበለ፡ | ዐደን፣ |
| ነደፈ፡ | ነካታ፣ | ነቀሸ፡ | ሠነገ፡ | ዐባይ፣ | ዐደን፡ |
| ናወዘ፡ | ነኰተ፣ | ነቀተ፡ | ሠነጋ፡ | ዐበላ፣ | ዐደፈ፣ |
| ነወጠ፣ | ንምራ፣ | ናርጅ፡ | ሠንጋ፣ | ዐበረ፣ | ዐደፍ፡ |
| ነውጥ፡ | ነነዌ፡ | ነረተ፡ | ሠንጎ፣ | ዐቦሬ፣ | ዐደረ፣ |
| ነወረ፣ | ነፈገ፡ | ናረት፡ | ሠነቀ፡ | (ዐበረ) | ዐዳር፡ |
| ነውር፡ | ንፉግ፣ | ነሰበ፡ | ሥንቅ፣ | ዐቧራ፣ | ዕዳሬ፣ |
| ናወተ፡ | ነፈዘ፡ | ነሲብ፣ | ሥንቆ፡ | ዐገዘ፡ | ዕድር፣ |
| ነዘዘ፣ | ነፈዝ፡ | ነሸጠ፣ | ሣቀየ፡ | ዐጎዛ፣ | ዐደር፡ |
| ናዘዘ፡ | ናፈጠ፣ | ነሰረ፣ | ሥቃይ፣ | ዐገለ፣ | ዐደሬ፡ |
| ኑዛዜ፡ | ነፍጥ፣ | ነስር፣ | ሠረበ፣ | ዕግል፣ | ዐጀረ፣ |
| ነዘለ፣ | ንፍጥ፣ | ንስር፡ | ሢርባ፡ | ዐጉል፣ | ዐጅሬ፣ |
| ነዚፉ፣ | ናፈለ፡ | ነሸረ፡ | ሠረገ፡ | ዐገመ፡ | ዐደሰ፡ |
| ነዘረ፣ | ነፈል፣ | ነተበ፣ | ሢርጋ፡ | ዐገሠ፣ | ዐዲስ፣ |
| ነዝር፡ | ናፈቀ፡ | ንትብ፡ | ሠረዘ፡ | ዐገተ፣ | ዐወደ፣ |
| ናዘረ፣ | ንፍቅ፣ | ነተፈ። | ሠረዝ፡ | ዕጎቻ፡ | ዐውድ፣ |
| ናዜራ፡ | ነፈረ፡ | (ሠ) | ሠረጠ፡ | ዐጎት፡ | ዐወጀ፣ |
| ነሐሴ፡ | ንፍር፡ | ሠበዘ፣ | ሥርጥ፣ | ዐጓት፣ | ዐዋጅ፣ |
| ነጠበ፡ | ንፍሮ፣ | ሠበዝ፣ | ሠራጨ፡ | ዐጀበ፣ | ዐዋዜ፣ |
| ነጥብ፣ | ነፈሰ፣ | ሠገገ፣ | ሥረይ፡ | ዐጀብ፡ | ዐውሎ፡ |
| ነጠጠ፣ | ነፉስ፣ | ሠጋጊ፣ | ሥራይ፣ | ዐደገ፣ | ዐወቀ፣ |
| ነጠለ፡ | ነፍስ፡ | ሠገረ፣ | ሠርክ፣ | ዐደዳ፡ | ዐወረ፡ |
| ነጠላ፣ | ነፍት፣ | ሠጋር፡ | ሢራክ፡ | (ዐደየ) | ዐወሰ፡ |
| ነጠፈ፣(፩) | ነቀዘ፡ | ሠጠጠ፡ | ሠረቀ፣ | ዐደይ፣ | ዐዘበ፣ |
| ነጠቀ፡ | ነቀዝ፡ | ሣጠራ፡ | ሣረረ፡ | ዐደለ፡ | ዐዛባ፡ |
| ነጠረ፡ | ነቁጥ፣ | ሠየመ፡ | ሠተረ። | ዕድል፣ | ዐዘለ፡ |
| ንጥር፣ | ነቀለ፡ | ሡካር፣ | (ዐ) | ዐደሌ፣ | ዕዝል፣ |
| ነጥር፡ | ነቀላ፣ | ሠለጠ፣ | ዐበዘ፣ | ዐዳል፣ | ዐዘሎ፡ |
| ነጠሰ፣ | ነቀፈ፣ | ሠላጤ፡ | ዐበጠ፣ | ዐጀለ፣ | ዐዘነ፣ |
| ነከለ፡ | ነቀፋ፡ | ሣለቀ፡ | ዕባጭ፡ | ዐደመ፡ | ዐዘን፣ |
| ነከረ፣ | ነቀረ፡ | ሥላቅ፣ | ዐበጠ፣ | ዐድማ፣ | ዐጠበ፣ |
| ነኰረ፣ | ንቃሬ፣ | ሠለሰ፡ | ዐብጤ፡ | ዕድሜ፣ | ዐጠድ፣ |
| ነከሰ፣ | ነቄረ፡ | ሠላሳ፣ | ዐበየ፡ | ዐጀም፣ | ዐጨደ፣ |
| ንክሻ፣ | ነቋራ፡ | ሥላሴ፣ | ዐብዬ፡ | ዐደነ፣ | ዐጨዳ፣ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዐጠጠ፡ | ዐሉላ፡ | ዐማች፡ | ዐረጠ፡ | (ፈ) | ፎከት፡ |
| ዐጠጥ፡ | ዐለመ፡ | ዐነጠ፡ | ዐራጣ፡ | ፈገገ፡ | ፈለገ፡ |
| ዐጣጥ፡ | ዕልም፡ | ዐኘከ፡ | ዕሪያ፡ | ፈገጠ፡ | ፈለጓ፡ |
| ዐጥም፡ | ዐለመ፡ | ዕኝካ፡ | ዐርኬ፡ | ፉጐሎ፡ | ፍለጋ፡ |
| ዐጠነ፡ | ዓለም፡ | ዐነቀ፡ | ዐረመ፡ | ፈገመ፡ | ፈለጠ፡ |
| ዕጣን፡ | ዓላማ፡ | ዐሣማ፡ | ዐረም፡ | ፈጋራ፡ | ፈሊጥ፡ |
| ዐጠፈ፡ | ዐለፈ፡ | ዐሠሠ፡ | ዐረፈ፡ | ፉገረ፡ | ፈለለ፡ |
| ዐጠፉ፡ | ዐለቀ፡ | ዐሠር፡ | ዐረፉ፡ | ፏደደ፡ | ፈለመ፡ |
| ዐጥፍ፡ | ዐመገ፡ | ዐሥር፡ | ዕራፊ፡ | ፊደል፡ | ፈለማ፡ |
| ዐጠቀ፡ | ዐማጋ፡ | ዐፈነ፡ | ዕርፍ፡ | ፈደነ፡ | ፉልማ፡ |
| ዐጥቅ፡ | ዐመደ፡ | ዐፈና፡ | ዐረፉ፡ | ፉደት፡ | ፈለቀ፡ |
| ዐጨቀ፡ | ዐመድ፡ | ዐፈሠ፡ | ዐረቀ፡ | ፈወሰ፡ | ፈለሰ፡ |
| ዐጠረ፡ | ዐሞድ፡ | ዐፈሣ፡ | ዕርቅ፡ | ፈውስ፡ | ፈላሻ፡ |
| ዐጥር፡ | ዐሻዳ፡ | ዐፈረ፡ | ዐረረ፡ | ፈዘዘ፡ | ፈነዳ፡ |
| ዐጠረ፡ | ዐምድ፡ | ዐፉር፡ | ዐራራ፡ | ፈዛዛ፡ | ፍንጅ፡ |
| ዐጭር፡ | ዐመጠ፡ | ዐቀበ፡ | ዕራሪ፡ | ፈጠጠ፡ | ፍናጅ፡ |
| ዐይጥ፡ | ዐመጥ፡ | ዐቃቢ፡ | ዐረር፡ | ፈጣጣ፡ | ፈንዤ፡ |
| ዐየለ፡ | ዐሞጭ፡ | ዐቀደ፡ | ዐረሰ፡ | ፈጠጤ፡ | ፈነጠ፡ |
| ዐያሌ፡ | ዐመል፡ | ዐቅድ፡ | ዕርሻ፡ | ፈጠመ፡ | ፌንጣ፡ |
| ዐያል፡ | ዐምሌ፡ | ዐቅል፡ | ዐረሰ፡ | ፈጠም፡ | ፈነጨ፡ |
| ዐይን፡ | ዐመመ፡ | ዐቅም፡ | ዐራስ፡ | ፈጠነ፡ | ፉነነ፡ |
| ዐከበ፡ | ዕመም፡ | ዐቀፈ፡ | ዐሰበ፡ | ፈጣን፡ | ፎነነ፡ |
| ዐከከ፡ | ዐምና፡ | ዐቄረ፡ | ዐስብ፡ | ፎጠና፡ | ፈነረ፡ |
| ዕከክ፡ | ዐመቀ፡ | ዐረበ፡ | ዐሱብ፡ | ፈጠረ፡ | ፈንታ፡ |
| ዐከመ፡ | ዐማራ፡ | ዐሩብ፡ | ዐሸበ፡ | ፎጠረ፡ | ፈጸመ፡ |
| ዐኪም፡ | ዐማሮ፡ | ዐረበ፡ | ዐሰበ፡ | ፈየደ፡ | ፈቀደ፡ |
| ዐለበ፡(፫) | ዐመሰ፡ | ዐርብ፡ | ዐሳብ፡ | ፉይዳ፡ | ፈቃድ፡ |
| ዐሊብ፡ | ዐሙስ፡ | ዐረገ፡ | ዐሸለ፡ | ፈየጠ፡ | ፈቀቀ፡ |
| ዐላባ፡ | ዐምሳ፡ | ዐረጓ፡ | ዐሸመ፡ | ፍየል፡ | ፎቃቃ፡ |
| ዐልበ፡ | ዐመተ፡ | ዐረደ፡ | ዐሳር፡ | ፈከከ፡ | ፈቀረ፡ |
| ዐለጠ፡ | ዕመት፡ | ዐራጅ፡ | ዐሻሮ፡ | ፈከረ፡ | ፍቅር፡ |
| ዐልጫ፡ | ዐሞት፡ | ዐራዳ፡ | ዐሰት፡ | ፎከረ፡ | ፍርግ፡ |
| ዐለለ፡ | ዓመት፡ | ዐረዘ፡ | ዐተበ፡ | ፉከራ፡ | ፈረደ፡ |
| ዐለላ፡ | ዐማት፡ | ዕሪዝ፡ | ዐተመ። | ፎከተ፡ | ፍርድ፡ |

ፈርጅ ፡
ፍሪዳ ፡
ፈረጠ ፡
ፈርጥ ፡
ፈረመ ፡
ፊርማ ፡
ፈረቀ ፡
ፈረቃ ፡
ፈረሰ ፡
ፈርስ ፡
ፍራሽ ፡
ፍራሽ ፡
ፈረስ ፡
ፋሽገ ፡
ፈሰከ ፡
ፋሲካ ፡
ፋሽከ ፡
ፋሽኮ ፡
ፍሽካ ፡
ፈሶሌ ፡
ፈሰሰ ፡
ፈሳሽ ፡
ፈሰስ ፡
ፈሰሴ ፡
ፈተገ ፡
ፈተለ ፡
ፈትል ፡
ፈቸለ ፡
ፈቸል ፡
ፈተነ ፡
ፈተና ፡
ፈተረ ፡
ፈተሸ ፡
ፍተሻ ፡

ፈተተ ።
(ጸ)
ጸበበ ፡ (ጠ)
ጸደይ ፡
ጸደቀ ፡
ጻድቅ ፡
ጽድቅ ፡
ጸየፈ ፡
ጸያፍ ፡
ጸለየ ፡
ጸሎት ፡
ጽላት ።
(ፀ)
ፀሓይ ፡
ፀነሰ ፡ (ጠ)
(ቀ—ቈ)
ቈበበ ፡
ቈባባ ፡
ቃብዱ ፡
ቀበጠ ፡
ቀበጥ ፡
ቀበለ ፡
ቀበሌ ፡
ቀበሎ ፡
ቅበላ ፡
ቀበና ፡
ቀበረ ፡
ቀብር ፡
ቀበሮ ፡
ቈበር ፡
ቀደደ ፡
ቀደመ ፡
ቀድሞ ፡
ቅድም ፡

ቅዳሜ ፡
ቈደረ ፡
ቈደር ፡
ቀደሰ ፡
ቅዳሴ ፡
ቀውጢ ፡
ቀወሰ ፡
ቀውስ ፡
ቀዎት ፡
ቀዘበ ፡
ቀዘባ ፡
ቀዘዘ ፡
ቅዛዛ ፡
ቈዘመ ፡
ቍዘማ ፡
ቀዘነ ፡
ቃዘነ ፡
ቀዘፈ ፡
ቈዘረ ፡
ቀጠበ ፡
ቅጠባ ፡
ቈጠበ ፡
ቍጠባ ፡
ቀጠጠ ፡
ቈጠጠ ፡
ቍጣጥ ፡
ቍጫጭ
ቀጠለ ፡
ቀጠላ ፡
ቅጠል ፡
ቅጥል ፡
ቃጠለ ፡
ቃጥላ ፡
ቃጠሎ ፡

ቃጨለ ፡
ቃጭል ፡
ቀጤማ ፡
ቀጨማ ፡
ቀጨሞ ፡
ቅጫም ፡
ቀጠነ ፡
ቀጠና ፡
ቀጣና ፡
ቀጪኔ ፡
ቀጪን ፡
ቀጠፈ ፡
ቀጠፉ ፡
ቀጠረ ፡
ቅጥር ፡
ቃጠረ ፡
ቀጠሮ ፡
ቈጠረ ፡
ቍጥር ፡
ቋጠረ ፡
ቋጥር ፡
ቋጨራ ፡
ቈጠሰ ፡
ቍጢሶ ፡
ቀየደ ፡
ቀየጠ ፡
ቀየመ ፡
ቅያሜ ፡
ቀየረ ፡
ቀየሰ ፡
ቅያስ ፡
ቀለበ (፪)
ቀለብ ፡
ቀልብ ፡

ቀለደ ፡
ቀልድ ፡
ቀላድ ፡
ቀለዘ ፡
ቈለዘ ፡
ቀለጠ ፡
ቀለጥ ፡
ቀለጠ ፡
ቈለጥ ፡
ቈለጠ ፡
ቈለጭ ፡
ቀለለ ፡
ቀሊል ፡
ቀላል ፡
ቈለለ ፡
ቀለመ ፡
ቀለም ፡
ቀላማ ፡
ቈለፈ ፡
ቍልፍ ፡
ቀለሰ ፡
ቀለሽ ፡
ቀለተ ፡
ቃልቻ ፡
ቈመደ ፡
ቀመጠ ፡
ቈመጠ ፡
ቈመጥ ፡
ቈማጣ ፡
ቍምጣ ፡
ቋመጠ ፡
ቀመለ ፡
ቅማል ፡
ቀመመ ፡

ቅመም ፡
ቀመረ ፡
ቀመር ፡
ቍማር ፡
ቀመሰ ፡
ቅምሻ ፡
ቀሚስ ፡
ቀነዳ ፡
ቀንድ ፡
ቀንዳ ፡
ቀንጃ ፡
ቅናጅ ፡
ቋንጃ ፡
ቃንዛ ፡
ቀናጣ ፡
ቈነጠ ፡
ቈነጨ ፡
ቍንጫ ፡
ቀኖና ፡
ቈነነ ፡
ቀነፈ ፡
ቀነረ ፡
ቀነሰ ፡
ቈነሰ ፡
ቍናስ ፡
ቀነተ ፡
ቅናት ፡
ቀሠጠ ፡
ቀሠመ ፡
ቀሠም ፡
ቀሠፈ ፡
ቀሠረ ፡
ቀፈደ ፡
ቀፈድ ፡

ቈፈነ፡
ቈፈን፡
ቀፈፈ፡ (፫)
ቀፈረ፡
ቈፈረ፡
ቍፈራ፡
ቍፋሮ፡
ቀፈት፡
ቀቀለ፡
ቀቀረ፡
ቈቀር፡
ቀቀተ፡
ቅቅት፡
ቋቅቻ፡
ቀረበ፡
ቅርብ፡
ቈረበ፡
ቍርባ፡
ቍርዝ፡
ቀረጠ፡
ቀረጥ፡
ቈረጠ፡
ቈራ’ጥ፡
ቍርዬ፡
ቈርኬ፡
ቃረመ፡
ቈረመ፡
ቀረና፡
ቅራና፡
ቈረነ፡
ቈረን፡
ቈረኝ፡
ቍራኛ፡
ቀረፈ፡

ቀረፋ፡
ቈረፈ፡
ቋርፍ፡
ቀረረ፡
ቅራሪ፡
ቈረረ፡
ቈረሰ፡
ቅርስ፡
ቀረሸ፡
ቈሸበ፡
ቈሰለ፡
ቍስል፡
ቀሰሰ፡
ቈሰሰ፡
ቈሸሸ፡
ቈሻሻ፡
ቀሰተ፡
ቀስት፡
ቋትል፡
ቈተመ፡
ቀተረ፡
ቀትር፡
ቋቲሮ፡
ቀተራ፡
ቃተተ፡
ቈተቸ፡
ቍትቻ።

(ረ)

ረበበ፡
ረበደ፡
ረባዳ፡
ረብጣ፡
ረበከ፡
ረበተ፡

ረገበ፡
ርግብ፡
ረገደ፡
ረገድ፡
ረገዘ፡
ርጉዝ፡
ረገጠ፡
ርግጫ፡
ርግጥ፡
ረገመ፡
ረገፈ፡
ርጋፊ፡
ርጋፎ፡
ረድፍ፡
ረዘመ፡
ረዥም፡
ረጠበ፡
ርጥብ፡
ረጠጠ፡
ረከበ፡
ርካብ፡
ረኸጥ፡
ርኩም፡
ረከሰ፡
ርኩስ፡
ርካሽ፡
ርኮት፡
ረኮተ፡
ረመደ፡
ርምጃ፡
ርምድ፡
ረመጠ፡
ረመጥ፡
ርሚጠ፡

ረሞጫ፡
ራመመ፡
ረመሰ፡
ሮምታ፡
ረፈደ፡
ረፋድ፡
ረፈቀ፡
ረቀቀ፡
ረቂቅ፡
ርሳስ።

(ሰ–ሸ)

ሰበብ፡
ሸበበ፡
ሸበድ፡
ሽብዳ፡
ሽባጥ፡
ሰበከ፡
ሰበካ፡
ሰብል፡
ሸበላ፡
ሰበን፡
ሰበቀ፡
ሰብቅ፡
ሰበረ፡
ሸበረ፡
ሽብር፡
ሰበተ፡
ስበት፡
ሸበተ፡
ሽበት፡
ሰገባ፡
ሸጐበ፡
ሰገደ፡
ሰገድ፡

ሰጐደ፡
ሰገጠ፡
ሰገጥ፡
ሰጐጥ፡
ሸጐጠ፡
ሸጕጥ፡
ሰገል፡
ሰገሌ፡
ሰጐን፡
ሸገነ፡
ሸገና፡
ሻገረ፡
ሸጐረ፡
ሻጕራ፡
ሻገተ፡
ሻጋታ፡
ሰደበ፡
ስድብ፡
ሰደደ፡
ሰደድ፡
ሰደፍ፡
ሰዲቃ፡
ሰደረ፡
ሴደር፡
ሸውክ፡
ሰወረ፡
ሰሐራ፡
ሰጠመ፡
ሰጥር፡
ሰየመ፡
ሰየፈ፡
ሰይፍ፡
ሰከከ፡
ሲካካ፡

ሾከከ፡
ሾካካ፡
ሰከለ፡
ሰካላ፡
ሳክላ፡
ሸክላ፡
ሻክላ፡
ሰኰመ፡
ሸከመ፡
ሸክም፡
ሰከነ፡
ሰኰና፡
ሽክና፡
ሸከፈ፡
ሰከረ፡
ሰካር፡
ስካር፡
ሻከረ፡
ሻካራ፡
ሻኹራ፡
ሰለበ፡
ሰለባ፡
ሸለበ፡
ሶለግ፡
ሸለገ፡
ስልጃ፡
ሹልዳ፡
ሰሊጥ፡
ሽልጠ፡
ሰለከ፡
ስልክ፡
ሾለከ፡
ሰለለ፡
ስለላ፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰለለ ፡ | ሰሞን ፡ | ሰፈፍ ፡ | ሽርጥ ፡ | ተገነ ፡ | ተመገ ፡ |
| ሰላላ ፡ | ሸማኔ ፡ | ሸፈፈ ፡ | ሰረየ ፡ | ተገን ፡ | ተመመ ፡ |
| ሰላሌ ፡ | ሸመቀ ፡ | ሸፋፋ ፡ | ሸረከ ፡ | ችግኝ ፡ | ተመን ፡ |
| ሸለለ ፡ | ሰመረ ፡ | ሽፉፍ ፡ | ሸሪክ ፡ | ትግሬ ፡ | ተምር ፡ |
| ሽለላ ፡ | ሰመር ፡ | ሰፈረ ፡ | ሰርን ፡ | ቸገረ ፡ | ቱማታ ፡ |
| ሰለመ ፡ | ስሙር ፡ | ሰፈር ፡ | ሶረን ፡ | ችግር ፡ | ተምች ፡ |
| ሰላም ፡ | ሰማራ ፡ | ስፍራ ፡ | ሰርፍ ፡ | ችጋር ፡ | ተነነ ፡ |
| ሸለመ ፡ | ሸመተ ፡ | ስፍር ፡ | ሸረፈ ፡ | ተከዘ ፡ | ትንኝ ፡ |
| ሽልሜ ፡ | ሸመታ ፡ | ሸፈተ ፡ | ሸረፋ ፡ | ትካዜ ፡ | ቸነነ ፡ |
| ሰሌን ፡ | ሳንባ ፡ | ሽፍታ ፡ | ሰረቀ ፡ | ተከዚ ፡ | ቸንች ፡ |
| ሰለፈ ፡ | ሰነባ ፡ | ሸፍት ፡ | ስርቅ ፡ | ተከለ ፡ | ቸፈገ ፡ |
| ሰልፍ ፡ | ሰነድ ፡ | ሽቅብ ፡ | ሰረረ ፡ | ተክል ፡ | ቸፈረ ፡ |
| ሸለፈ ፡ | ሰናዳ ፡ | ሸቀበ ፡ | ሸረረ ፡ | ቸከለ ፡ | ተረበ ፡ |
| ሰለቀ ፡ | ስንዴ ፡ | ሸቃበ ፡ | ሰሪቴ ፡ | ችካል ፡ | ተረብ ፡ |
| ሸለቆ ፡ | ሸንዳ ፡ | ሰቀዘ ፡ | ሸሸገ ፡ | ተኰላ ፡ | ተርብ ፡ |
| ሾለቅ ፡ | ሰነጠ ፡ | ሰቀጠ ፡ | ሴሰየ ፡ | ቸኰለ ፡ | ቶረበ ፡ |
| ሰለተ ፡ | ሽንጥ ፡ | ሰቃጢ ፡ | ሲሳይ ፡ | ችኰላ ፡ | ተረከ ፡ |
| ሰለታ ፡ | ሰንጢ ፡ | ሸቀጠ ፡ | ሰሰለ ፡ | ተከነ ፡ | ታሪክ ፡ |
| ስልት ፡ | ስናጭ ፡ | ሸቀጥ ፡ | ሴሰነ ፡ | ተኰነ ፡ | ተረፈ ፡ |
| ስልቻ ፡ | ስንኝ ፡ | ሰቄጣ ፡ | ሴሰን ፡ | ትኳን ፡ | ትራፊ ፡ |
| ሰለቸ ፡ | ሰነፈ ፡ | ሰቀለ ፡ | ሴሰኛ ፡ | ተከረ ፡ | ተረፍ ፡ |
| ስልቹ ፡ | ሰነፍ ፡ | ሰቀላ ፡ | ሾተለ ፡ | ተኰረ ፡ | ተረረ ፡ |
| ሸለተ ፡ | ሸነፈ ፡ | ሸቀን ፡ | ሾተል ፡ | ተኳር ፡ | ተራራ ፡ |
| ሸለታ ፡ | ሲናር ፡ | ሰቀቀ ፡ | ሳተነ ፡ | ተኰሰ ፡ | ቸረረ ፡ |
| ሰመግ ፡ | ስናር ፡ | ሸረበ ፡ | ሳተና ፡ | ተኰስ ፡ | ተረተ ፡ |
| ሰመጎ ፡ | ስንት ፡ | ሹራብ ፡ | ሳተፈ ፡ | ታከተ ፡ | ተረት ፡ |
| ሸመደ ፡ | ሽንት ፡ | ሹርባ ፡ | ሸተረ ፡ | ተልባ ፡ | ቸሰረ ፡ |
| ስምዛ ፡ | ሰፌድ ፡ | ሾርባ ፡ | ሻተረ ፡ | ተለለ ፡ | ተተገ ፡ |
| ሰመጠ ፡ | ሻፈደ ፡ | ሰረገ ፡ | ሰታቴ ፡ | ተለላ ፡ | ታታረ ፡ |
| ሸመጥ ፡ | ሸፈጠ ፡ | ሰርግ ፡ | ሸተተ ፡ | ተላላ ፡ | ቸቸረ ። |
| ሰማይ ፡ | ሸፍጥ ፡ | ሰርዶ ፡ | ሻተተ ። | ተለመ ፡ | (ጸ) |
| ሸመመ ፡ | ሽፋል ፡ | ሰረጀ ፡ | (ተ—ቸ) | ታልማ ፡ | ጸጸስ ። |
| ሸማማ ፡ | ሸፈነ ፡ | ሸረጠ ፡ | ተገበ ፡ | ትለም ፡ | (ፐ) |
| ሰመነ ፡ | ሰፈፈ ፡ | ሸርጥ ፡ | ተግብ ፡ | ቸለሰ ፡ | ፓሪስ ። |

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ያራት ፡ ፊደል ፡ ግስ ፤ (በደጊመ ፡ ቃል) ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| (አ) | ገውጋዋ ፡ | ገረገረ ፡ | ደነደነ ፡ | ዘምዘም ፡ |
| አፍኣዊ ። | ገዘገዘ ፡ | ገረገራ ፡ | ደንዳና ፡ | ዘነዘና ፡ |
| (በ) | ግዝጋዛ ፡ | ግርግር ፡ | ደንዳኔ ፡ | ዘፈዘፈ ፡ |
| በገበገ ፡ | ጎዘጎዘ ፡ | ጎረጎረ ፡ | ድንድን ፡ | ዘቀዘቀ ፡ |
| በደበደ ፡ | ጕዝጓዝ ፡ | ጕርጓሮ ፡ | ደፈደፈ ፡ | ዠቀዠቀ ፡ |
| በዘበዘ ፡ | ገጠገጠ ፡ | ገሸገሸ ፡ | ድፍድፍ ፡ | ዘረዘረ ፡ |
| ብዝበዛ ፡ | ጎጠጎጠ ፡ | ገተገተ ፡ | ዶፈዶፈ ፡ | ዝርዝር ፡ |
| በጠበጠ ፡ | ገጨገጨ ፡ | ጎተጎተ ፡ | ዶፍዱፉ ፡ | ዝርዝ'ር ፡ |
| ብጥበጣ ፡ | ገለገለ ፡ | ጕትጎታ ፡ | ደቀደቀ ፡ | ዠረዠረ ፡ |
| ቦጠቦጠ ፡ | ግልጋሎ ፡ | ገችጋቻ ። | ደረደረ ። | ዘተዘተ ። |
| ቦከቦከ ፡ | ገላገለ ፡ | (ደ–ጀ) | (ወ) | (ጠ–ጨ) |
| በለበለ ፡ | ግልግ'ል ፡ | ደበደበ ፡ | ወዘወዘ ፡ | ጠበጠበ ፡ |
| ቦፈቦፈ ፡ | ግልግል ፡ | ድብደባ ፡ | ውዝዋዜ ፡ | ጥብጠባ ፡ |
| በቀበቀ ፡ | ጓልገል ፡ | ድብድብ' ፡ | ወጠወጠ ፡ | ጥብጣብ ፡ |
| ቦረቦጭ ፡ | ጎለጎለ ፡ | ድብዳብ ፡ | ወከወከ ፡ | ጨበጨበ ፡ |
| በረበረ ፡ | ጕልጓሎ ፡ | ደብዳቤ ፡ | ወለወለ ፡ | ጭብጨባ ፡ |
| በርበራ ፡ | ገመገመ ፡ | ደሰደበ ፡ | ወላወለ ፡ | ጠዘጠዘ ፡ |
| በርበሬ ፡ | ጓምገማ ፡ | ጀብጀባ ፡ | ወነወነ ፡ | ጠለጠለ ፡ |
| በርበር ፡ | ገነገነ ፡ | ደገደገ ፡ | ወረወረ ፡ | ጠልጣላ ፡ |
| ብርበራ ፡ | ግንገና ፡ | ደግዳጋ ፡ | ውርወራ ፡ | ጦለጦለ ፡ |
| ብርብራ ፡ | ጎነጎነ ፡ | ድግድግ ፡ | ወሰወሰ ፡ | ጦልጧላ ፡ |
| ቦረቦረ ፡ | ጕንጕን ፡ | ዶገዶገ ፡ | ወተወተ ፡ | ጨለጨለ ፡ |
| በሰበሰ ፡ | ገሠገሠ ፡ | ደዘደዘ ፡ | ውትወታ ። | ጠመጠመ ፡ |
| በተበተ ። | ግሥግሣ ፡ | ደከደከ ፡ | (ዘ–ዠ) | ጥምጥም ፡ |
| (ገ–ጐ) | ጎሠጎሠ ፡ | ደለደለ ፡ | ዘበዘበ ፡ | ጨመጨመ |
| ገበገበ ፡ | ገፈገፈ ፡ | ደልዳላ ፡ | ዝብዘባ ፡ | ጨምጨሞ፡ |
| ገብጋባ ፡ | ጎፈጎፈ ፡ | ድልድል ፡ | ዘጠዘጠ ፡ | ጠፈጠፈ ፡ |
| ጎበጎበ ፡ | ጎፍጓፉ ፡ | ዶለዶለ ፡ | ዘጥዛጣ ፡ | ጠፍጣፋ ፡ |
| ገደገደ ፡ | ገረገበ ፡ | ዶልዱላ ፡ | ዠጠዠጠ ፡ | ጥፍጥፍ ፡ |
| ግድግዳ ፡ | ገረገመ ፡ | ዶልዱሌ ፡ | ዘከዘከ ፡ | ጠፈጠፍ ፡ |
| ጎደጎደ ፡ | ጓርግም ፡ | ዶለዶመ ፡ | ዘለዘለ ፡ | ጨፈጨፈ ፡ |
| ጎድጓዳ ፡ | ጎረጎመ ፡ | ዶልዱማ ፡ | ዠለዠለ ፡ | ጨፈጨፍ ፡ |
| ጕድጓድ ፡ | ጎረጎማ ፡ | ደመደመ ፡ | ዘመዘመ ፡ | ጠቀጠቀ ፡ |

ጠቃጠቆ ፣
ጨቀጨቀ ፣
ጭቅጭቅ ፣
ጠረጠረ ፣
ጥርጥር ፣
ጥርጣሬ ፣
ጠራጠር ፣
ጨረጨረ ፣
ጨርጨር ፣
ጠሰጠሰ ።

(ከ–ኰ)

ከበከበ ፣
ኰበኰበ ፣
ኰብኰባ ፣
ከውካዋ ፣
ከለከለ ፣
ኰለኰለ ፣
ከመከመ ፣
ክምክም ፣
ኰመኰመ ፣
ከነከነ ፣
ክንካኔ ፣
ከፈከፈ ፣
ኰፈኰፈ ፣
ከረከረ ፣
ክርክ'ር ፣
ክርክር ፣
ከርከር ፣
ከርከሮ ፣
ኰረኰረ ፣
ኵርኰራ ፣
ከሰከሰ ፣
ከስከሶ ፣
ከሽከሽ ፣
ኰሰኰሰ ፣
ኰሸኰሸ ፣
ኰሽኰሽ ፣
ከተከተ ፣
ክትክታ ፣
ኰተኰተ ።

(ለ)

ለበለበ ፣
ልብለባ ፣
ለገለገ ፣
ለግላጋ ፣
ለደለደ ፣
ለድላዳ ፣
ለውላዋ ፣
ለዘለዘ ፣
ለጠለጠ ፣
ሎጥሏጣ ፣
ለከለከ ፣
ለመለመ ፣
ልምላሜ ፣
ለፈለፈ ፣
ልፍለፋ ፣
ለቀለቀ ፣
ልቅለቃ ፣
ለሰለሰ ፣
ልስልስ ፣
ለሸለሸ ፣
ለተለተ ፣
ለትላታ ።

(መ)

መገመገ ፣
መደመደ ፣
መደመድ ፣
ሞደሞደ ፣
መዘመዘ
ምዝምዝ ፣
መጠመጠ ፣
ሚጥሚጣ ፣
ሞጠሞጠ ፣
ሞጥሟጣ ፣
መጨመጨ
መጭማጫ ፣
መከመከ ፣
መክማኪ ፣
መለመለ ፣
ምልመላ ፣
መነመነ ፣
መንማና ፣
መቀመቀ ፣
ሞቀሞቀ ፣
መቅመቆ ፣
መረመረ ፣
ምርምር ፣
ምርመራ ፣
መረመር ፣
ሞረሞረ ።

(ነ)

ነበነበ ፣
ነገነገ ፣
ነዘነዘ ፣
ነዝናዛ ፣
ንዝናዜ ፣
ንዝንዝ ፣
ነጠነጠ ፣
ነጨነጨ ፣
ነጭናጫ ፣
ነከነከ ፣
ነፈነፈ ፣
ነቀነቀ ፣
ነሰነሰ ።

(ሠ)

ሠረሠረ ፣
ሠረሠር ፣
ሥርሥራ ።

(ፈ)

ፈገፈገ ፣
ፈደፈደ ፣
ፍድፋጅ ፣
ፈጠፈጠ ፣
ፈጨፈጨ ፣
ፈከፈከ ፣
ፎከፎከ ፣
ፈለፈለ ፣
ፍልፈፍ ፣
ፈነፈነ ፣
ፈቀፈቀ ፣
ፈረፈረ ፣
ፈረፈር ፣
ፍርፋሪ ፣
ፈሰፈሰ ፣
ፎሸፏሻ ፣
ፈተፈተ ፣
ፍትፍት ።

(ቀ)

ቀበቀበ ፣
ቅብቃብ ፣
ቅብቅብ ፣
ቈበቈበ ፣
ቀውቃዋ ፣
ቀዘቀዘ ፣
ቀዝቃዛ ፣
ቅዝቃዜ ፣
ቀዠቀዠ ፣
ቀዥቃዣ ፣
ቀጠቀጠ ፣
ቀጥቃጣ ፣
ቅጥቅጥ ፣
ቈጠቈጠ ፣
ቍጥቋጠ ፣
ቀጨቀጨ ፣
ቀጨቀጭ ፣
ቈጨቈጨ ፣
ቈጭቋጫ ፣
ቀለቀለ ፣
ቀለቀል ፣
ቀልቃላ ፣
ቀልቀሎ ፣
ቀላቀለ ፣
ቅልቅል ፣
ቈለቈለ ፣
ቈለቈል ፣
ቍልቍል ፣
ቍልቋል ፣
ቀመቀመ ፣
ቀምቀሞ ፣
ቀነቀነ ፣
ቅንቅን ፣
ቈነቈነ ፣
ቈንቋና ፣
ቀፈቀፈ ፣
ቈፈቈፈ ፣
ቀረቀበ ፣
ቀርቃባ ፣
ቀረቀረ ፣
ቅርቃር ፣
ቈረቈረ ፣

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቈረቈር ፣ | ረመረመ ፣ | ሸጠሸጠ ፣ | ሰቀሰቀ ፣ | ተፈተፈ ፣ |
| ቈርቈሮ ፣ | ረፈረፈ ፣ | ሰከሰከ ፣ | ስቅስቆ ፣ | ትፍትፍ ፣ |
| ቍርቍራ ፣ | ረቀረቀ ፣ | ሶከሶከ ፣ | ሸቀሸቀ ፣ | ቸፈቸፈ ፣ |
| ቀሰቀሰ ፣ | ረሰረሰ ፣ | ሸከሸከ ፣ | ሸረሸረ ። | ችፍችፍ ፣ |
| ቅስቃሴ ፣ | ረተረተ ። | ሰለሰለ ፣ | (ተ—ቸ) | ተረተረ ፣ |
| ቈሰቈሰ ። | (ሰ—ሸ) | ሰልሳላ ፣ | ተበተበ ፣ | ተረተር ፣ |
| (ረ) | ሰበሰበ ፣ | ሸለሸል ፣ | ቸበቸበ ፣ | ቸረቸረ ፣ |
| ረበረበ ፣ | ሰበሰብ ፣ | ሶመሶመ ፣ | ቸብቸቦ ፣ | ችርቻሮ ፣ |
| ርብራብ ፣ | ስብሳብ ፣ | ሱምሶማ ፣ | ተገተገ ፣ | ተሰተሰ ፣ |
| ርብርብ ፣ | ሸበሸበ ፣ | ሸመሸመ ፣ | ተከተከ ፣ | ቸሰቸሰ ። |
| ረገረገ ፣ | ሽብሽባ ፣ | ሽምሽም ፣ | ቸከቸከ ፣ | |
| ረግረግ ፣ | ሽብሽቦ ፣ | ሰነሰነ ፣ | ተለተለ ፣ | |
| ረዘረዘ ፣ | ሰገሰገ ፣ | ሸነሸነ ፣ | ተመተመ ፣ | |
| ርዝራዥ ፣ | ሸገሸገ ፣ | ሽንሽን ፣ | ቸመቸመ ፣ | |
| ረጠረጠ ፣ | ሸደሸደ ፣ | ሰፈሰፈ ፣ | ችምችም ፣ | |
| ረከረከ ፣ | ሸውሻዋ ፣ | ሰፍሳፋ ፣ | ተነተነ ፣ | |
| ርክርክ ፣ | ሰጠሰጠ ፣ | ሸፈሸፈ ፣ | ትንትና ፣ | |

(ፈ-ተና) ራሴን ፡ በራሴ ፡
ካላንቆላጰላጠስኹት ፡ ማ
ን ፡ ያንቆላጰላጥስልኛል ።

ምዕራፍ ፣ ፬ ።

የ፫ና ፣ ያ፬ ፡ ፊደል ፣ ግስ ፤ በሥሩ ፡ ልማድና ፣ ባዕድ ፤ በማኄ ፡ ዝርዝር ፣ ምእላድ ፡ ሲገባበት ፣ ፬ና ፣ ፭ ፡ ፮ና ፣ ፯ ፣ ፰ና ፡ ፱ ፣ ፲ም ፣ ይኾናል ። ይኸውም ፣ እንዲኽ ፣ ነው ።

ጠየቀ ፡

ተጠየቀ ።

መረመረ ፡

ተመረመረ ፡

አስመረመረ ፡

ተመራመራቸው ፡

አላስመረመረም ፡

አስመርምሯቸዋል ፡

አያስመረምራቸውም ።

ክፍል ፡ ፱ ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ።

ዐቈር ፣ የርባታ ፣ መቅድምና ፣ ዐዋጅ ።

(ተረት) ፤ ነገር ፣ ከሥሩ ፣ ውሃ ፡ ከጥሩ ።

ረቢሕ ፤ ረቢሖት ፡ (ረብሐ ፡ ይረብሕ ፡ ይርባሕ) ፡ መርባት ፣ መብዛት ። ርባሕ ፤ ርባ ፣ ርባታ ፤ አረባብ ፣ አበዛዝ ።

ርባታ ፣ በ፫ ፣ ዐይነት ፣ ክፍል ፣ ይከፈላል ፤ በወንድና ፣ በሴት ፤ ባንድና ፣ በብዙ ፡ በቅርብና ፣ በሩቅ ፤ መደበኛው ፣ ወንድና ፡ ሴት ፣ ነው ፤ አንድና ፣ ብዙ ፣ ቅርብና ፣ ሩቅ ፣ ከዚያው ፣ ይገባሉ ። በርባታም ፣ ውስጥ ፣ ፫ጊዜ ፣ አለ ፤ ያለፈና ፣ ያኹን ፣ የሚመጣ ። ያማርኛ ፣ ርባታ ፣ መደቡ ፣ ፱ ፣ ብቻ ፣ ነው ፤ ፮ቱ ፣ ያንዳንድ ፤ ፫ቱ ፣ የብዙ ። ፮ቱ ፣ የቅርብ ፤ ፫ቱ ፣ የሩቅ ። የብዙዎቹ ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ አንቀጻቸውም ፣ ዝርዝራቸውም ፣ በጥፈትና ፣ ባነጋገር ፣ ፩ቃል ፣ ኹኖ ፡ ኹለቱ ፣ ስላንድ ፣ ይቈጠራል ፤ እንደ ፣ ግእዝ ፣ ልዩነት ፣ የለውም ። ያንቱታውም ፣ ዝርዝርና ፣ አንቀጽ ፣ እንደ ፣ አንና ፣ እንደ ፣ ንሕን ፣ ወንድና ፣ ሴት ፡ ያስተባብራል ።

በባሕርይ ፣ ስም ፡ ፈንታ ፡ የሚነገር ፣ ፱ኙ ፣ ያካል ፣ ስም ፤ ወይም ፣ ቅጽልና ፣ ዐጸፋ ፣ የርባታ ፣ መደብ ፤ ከነሥሩና ፣ ከነምንጩ ።

### ም ን ጭ ።

ርኢስ ፤ ርኢሶት ፡ (ርእሰ ፡ ይርእስ ፡ ይርአስ) ፡ ራስ ፡ መኾን ። ርእስ ፤ ርስ ፥ ራስ ፡ የናላ ፡ ቅል ። ባለቤት ፡ ጌታ ፥ ገዥ ፡ አዛዥ ፤ ራሱን ፡ የቻለ ፥ ለራሱ ፡ የበቃ ፥ ለብቻው ፡ የቆመ ፡ የተለየ ፤ አካሌ ፡ የሚባል ፥ ወይም ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ነባቢ ፡ አካል ። ባለቤት ፡ ሲባል ፥ ባለ ፥ ነፍስን ፤ ቤት ፥ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከግር ፡ ጥፍር ፡ ያለ ፡ ሥጋን ፤ በተገናኝ ፡ ፍጹም ፡ ሰውነትን ፡ አካልን ፡ ቁመትን ፡ ነባቢነትን ፡ ያሳያል ። ርባታውና ፡ ዝርዝሩም ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ኹኖ ፡ በስምነቱ ፡ ላይ ፡ አካልና ፡ አንቀጽ ፡ እያሳየ ፡ በውእቱ ፡ መንገድ ፡ ይሄዳል ። የግስ ፡ መብቀያ ፡ ሥር ፡ መሠረቱ ፡ ባንድ ፡ በፍጹም ፡ በሩቅ ፡ ወንድ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ርባታውም ፡ በዚያው ፡ በሩቁ ፡ ወንድ ፡ በበቀለበት ፡ ዐምድ ፡ ይዠመራል ። ይኸውም ፡ ልማድ ፥ ርባታን ፡ በሩቅ ፡ ወንድ ፡ መዠመር ፡ የግእዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ሌላው ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ በራሱ ፡ በቅርቡ ፡ እኔ ፡ በሚለው ፡ ይዠምራል ።

### አ ን ዳ ን ዶ ች ።

(ሩቅ ፡ ወንድ)

**ርሱ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ቅሉ ፡ ባለቤቱ ፡ እንቶ ፡ ያ ።**

(ሩቅ ፡ ሴት)

**ርሷ ፡ እሷ ፡ ራሷ ፡ ቅሏ ፡ ባለቤቷ ፡ (እንትኩ) ፡ ያች ።**

(ቅርብ ፡ ወንድ)

**ርስኽ ፡ እስኽ ፡ ራስኽ ፡ ቅልኽ ፡ ባለቤትኽ ፡ አንተ ።**

(ቅርብ ፡ ሴት)

**ርስሽ ፡ እስሽ ፡ ራስሽ ፡ ቅልሽ ፡ ባለቤትሽ ፡ አንቺ ፡ ቺ ።**

(ነባቢ ፡ ወነባቢት) ወንድና ፡ ሴት)

**ርሴ ፡ እሴ ፡ ራሴ ፡ ቅሌ ፡ ባለቤቴ ፡ እኔ ፤ እኔው ።**

(ክቡርና ፡ ክብርት ፡ ወንድና ፡ ሴት)

**ርስዎ ፡ ኹ ፤ እስዎ ፡ ኹ ፤ ራስዎ ፡ ኹ ፤ ቅልዎ ፡ ኹ ፤ ባለቤትዎ ፡ ኹ ፤ አንቱ ።**

(ብዙዎች ፡ ሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፤ ወይም ፡ አንዳንዶች ፡ የሩቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በቅርብ ፡ ርስዎና ፡ አንቱ ፡ የሚባሉት)

**ርሳቸው ፡ እሳቸው ፡ ራሳቸው ፡ ቅላቸው ፡ ባለቤታቸው ፡ እኒያ ፡ እሊያ ።**

(ቅርቦች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች)

**ርሳችኹ ፡ እሳችኹ ፡ ራሳችኹ ፡ ቅላችኹ ፡ ባለቤታችኹ ፡ እና(ላ)ንተ ፡ ት ።**

(ነባብያን ፡ ወነባብያት) ወንዶችም ፡ ሴቶችም)

**ርሳችን ፡ እሳችን ፡ ራሳችን ፡ ቅላችን ፡ ባለቤታችን ፡ እኛ ።**

ከነዚኹ ፡ ደግሞ ፡ ለመደብነት ፡ ተመርጠው ፡ የወጡ ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ስሞች ፤
ወይም ፡ የመደበኛ ፡ ስም ፡ ምትኮች ።

ርሱ ፡ } ርሳቸው ።
ርሷ ፡ }

አንተ ፡ } እና(ላ)ንተ ።
አንቺ ፡ }

እኔ ፡ } እኛ ።
ርስዎ ፡ }

(ሐተታ) እኔ ፡ እኛ ፡ ከሚለው ፡ በቀር ፡ ፪ቱ ፡ ስም ፡ ተጠሪ ፡ ወኪል ፡ ይባላል ፤ ቶፋ ፡ እን ደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከ፪ቱ ፡ ደግሞ ፡ ቅርብ ፡ ቅርቡ ፡ በተጠሪነት ፡ ላይ ፡ ሰሚ ፥ ወይም ፡ ሰሚና ፡ ተጠሪ ፡ ይባላል ። እኔና ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ለብቻው ፡ ጠሪ ፥ ተናጋሪ ፡ ይባላል ፤ ዋና ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ርስዎ ፡ ማለት ፡ ቅርብ ፡ ኹኖ ፡ ምንም ፡ ካንዳንዶች ፡ ጋር ፡ ቢቈጠር ፥ አንቀጹ ፡ የብዙ ና ፡ የሩቅ ፡ ነውና ፡ የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ መስሎ ፡ ከርሳቸው ፡ ይገባል ። ርሱና ፡ ርሷ ፡ ርሳቸው ፥ እኒ ኽ ፡ ፫ቱ ፡ ደግሞ ፡ የሩቅ ፡ ብቻ ፡ ኹነው ፡ አይቀሩም ፤ የቅርብ ፡ ሩቅም ፡ ይኾናሉ ፤ ጥቂት ፡ ፈቀ ቅ ፡ ብሎ ፡ በዙሪያ ፡ በኋላ ፡ በስተቀኝና ፡ በስተግራ ፡ ያለ ፥ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሊያዩት ፡ ሊሰሙትና ፡ ሊናገሩት ፡ ሊጠሩትና ፡ ሊጠቅሱት ፡ የሚቻል ፥ በአንተ ፡ አንጻር ፡ ርሱ ፡ ይባላል ። (ርሱ ፡ ራሱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እን ፡ እየጨመሩ ፡ እርሱ ፡ እራሱ ፡ ማለት ፡ እርስት ፡ እሩብ ፡ እንደሚሉት ፡ ያ ለ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ። እሱ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ርእስ ፡ ካለው ፡ ከ፫ቱ ፡ ፊደላት ፡ ርን ፡ ውጦና ፡ ጕርዶ ፡ ነውና ፤ ርትዕ ፡ እንጂ ፡ ጸያፍ ፡ አይባልም) ። አንተና ፡ አንቺ ፡ እናንተና ፡ ርስዎ ፥ እኒኽ ፡ ፬ቱ ፡ በግንባር ፡ በአንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያሉ ፥ ባይን ፡ ተቀምለው ፡ በጣት ፡ ተጠንቍለው ፡ የሚታዩ ፡ የሚነገሩ ፡ ቅርቦች ፡ አጠገቦች ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ቅርቦች ፡ ይባላሉ ። እኔና ፡ እኛም ፡ እነዚኽ ፡ ኹለቱ ፡ ቅርቦች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ የአንተና ፡ የአንቺ ፡ የናንተ ፡ አንጻር ፡ ናቸው ። ዳግመኛም ፡ በ ነዚኽ ፡ በዘጠኙ ፡ ላይ ፡ በሥርና ፡ በጫፍ ፡ እየገቡ ፡ የቋንቋን ፡ ስልት ፥ የነገርን ፡ ብልት ፥ የርባታ ውን ፡ ዐምድ ፡ መንገድና ፡ አካሄድ ፡ ለይተው ፡ ለያይተው ፡ የሚያሳዩ ፡ አገባቦችና ፡ ዝርዝሮች ፡ አሉ ፤ ዝርዝሮቹ ፡ ኋላ ፡ ይመጣሉ ፥ አገባቦቹና ፡ ግቢያቸውም ፡ ከነስማቸው ፡ እሊኽ ፡ ናቸው ።

| (አገባብ) | (ግቢ) | (ስም) |
|---|---|---|
| የ | የርሱ ፡ | ጠቃሽ ። |
| ለ | ለርሱ ፡ | አቀባይ ። |
| በ | በርሱ ፡ | ማድረጊያ ። |
| ስለ ፡ | ስለ ፡ ርሱ ፡ | ምክንያት ። |
| ከ(ተ) | ከርሱ ፡ | መነሻ ። |
| ወደ ፡ | ወደ ፡ ርሱ ፡ | መገሥገሻ ። |
| እ | ዘንድ ፡ | እርሱ ፡ ዘንድ ፤ እስከ ፡ ርሱ ፤ መድረሻ ። |
| ን | ርሱን ፡ | (የገቢር) ተሳቢ ። |

(ሖተታ) መገሥገሻና ፡ መድረሻ ፣ አንድ ፣ ወገን ፡ ናቸው ፤ ይተባበራሉ ። እርሱ ፣ ዘንድ ፡ እስ ከ ፡ ርሱ ፣ በማለት ፡ ፈንታ ፣ እ ፣ ቀርቶ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከሱ ፣ ይባላል ፤ ይኸውም ፣ እና ፡ ከ ፣ አንድ ፡ ወገን ፣ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ፤ (ማስረጃ) የተጠማ ፡ ከፈሳሽ ፥ የተበደለ ፡ ከነጋሽ ። እና ፡ ከ ፣ ኹለቱም ፡ ከእስከ ፣ ተከፍለው ፡ የመጡ ፣ የእስከ ፡ ምልክት ፡ ናቸውና ፥ እ ፡ በሺዋ ፡ ዐማርኛ ፣ መገሥገሻና ፡ መድረሻ ፣ መኾኑ ፣ ስለዚኽ ፣ ነው ። መድረሻነቱ ፡ በቦታው ፣ ተነግሯል ፤ መገሥገሻ ፣ ሲኾን ፤ እቤት ፣ ግባ ፥ እደጅ ፡ ውጣ ። እ ፣ ማለት ፡ ስከን ፡ ጕርደ ፣ ነው ፥ ከ ፡ ማለትም ፡ እስን ፣ ጕርደ ፣ ነው ፤ በተገናኝ ፡ ኹሉም ፡ እስከ ፣ ማለት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ከ ፣ በ ፣ ይኾናል ፤ እግቢም ፡ እውጪም ፡ ፈልጌ ፣ ዐጣኹት ። ከ ፡ መነሻና ፡ በ ፡ ሲኾን ፣ አገባብነቱ ፡ ከእ ም ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፣ ከእስከ ፡ አይስማማም ።

ከደቂቅ ፡ ርባታ ፡ የወጣ ፣ የአካላዊ ፡ ስም ፣ ዝርዝርና ፣ ነባር ፡ አንቀጽ ፣ ከነዘማቹ ።

የዘማች ፣ ዝርዝር ፡ የሩቁ ፣ ኀላፊ ፥ ግእዝና ፡ ራብዕ ፣ (ዐየለ ፡ በረታ) ፤ ትንቢቱም ፥ የግእዙ ፣ ሳድስ ፥ የራብዑ ፣ ራብዕ ፡ (ያይል ፡ ይበረታ) ፡ ያስኛል ፤ የብዙዎቹ ፡ ግን ፡ ኹሉም ፣ ካዕብ ፡ ነው ።

| | (አካላዊ ፡ ስም) | (ዝርዝር) | (ነባር ፡ አንቀጽ) | (ዘማች ፡ አንቀጽ) |
|---|---|---|---|---|
| (ውእቱ) | ርሱ ፡ | ው | ነው ። | ገደለ ። |
| | ርሷ ፡ | ት ፡ ች | ናት ፡ ነች ። | ገደለች ። |
| | አንተ ፡ | ኽ ፡ ክ | ነኽ ። | ገደልኽ ፡ ክ ። |
| | አንቺ ፡ ቺ ፡ | ሽ | ነሽ ። | ገደልሽ ። |
| | እኔ ፡ | ኝ | ነኝ ። | ገደልኹ ፡ ኩ ። |
| | ርስዎ(አንቱ) | ዎ ፡ ኹ | ነዎ ፡ (ነኹ) ። | ገደሉ ፡ (ልኹ) |
| | ርሳቸው ፡ | ቸው | ናቸው ። | ገደሉ ። |
| | እና(ላ)ንተ ፡ | ችኹ | ናችኹ ። | ገደላችኹ ። |
| | እኛ ፡ | ነ ፡ ን | ነነ ፡ ነን ። | ገደልነ ፡ ን ። |

ያማርኛ ፡ ግስ ፣ ምሉ ፣ ሲኾን ፡ በ፯ ፣ አዕማድ ፥ ጕደሎ ፣ ሲኾን ፣ ከ፯ ፡ በታች ፣ እስከ፩ና ፣ እ ስከ፪ ፡ ድረስ ፣ በጕደሎነት ፡ ይረባል ። ከ፯ቱ ፡ አዕማድ ፡ ዋንኞቹ ፡ ፬ ፡ ናቸው ፤ ፫ቱ ፡ ግን ፣ ድር ቦችና ፡ ተወራጆች ፡ ወይም ፡ ተቀጥሎች ፡ ይባላሉ ፤ ምስጢራቸውም ፡ ነገር ፣ ማጽናትና ፣ ማበር ታት ፡ ነው ። ለነዚኽም ፡ ለ፯ቱ ፣ አዕማድ ፡ ልማድ ፡ የሚባሉ ፣ ፬ስከተቶች ፣ አሏቸው ፤ እሊኹም ፣ ራብዕ ፣ ስሯጽ ፤ አስ ፡ ተ ፡ አ ናቸው ። የአዕማዱም ፣ ረድፍና ፣ ተራ ፡ በየስከተቱና ፣ በየስሙ ፡ ይ ኽ ፣ ነው ። (ዘር ፡ ወይም ፡ ሥረ ፡ ነገር) **ቀቢር ፤ ቀቢሮት** ። መቅበር ፥ መቀባበር ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ኛ ፤ — **ቀበረ** ፡ | (ድርብ)— **ቀባበረ** ፡ | አድራጊ ። |
| ፪ኛ ፤ — **አስቀበረ** ፡ — | | አስደራጊ ። |
| ፫ኛ ፤ — **ተቀበረ** ፡ — | | ተደራጊ ፣ |
| ፬ኛ ፤ — **ተቃበረ** ፡ | (ድርብ)— **ተቀባበረ** ፡ | ተደራራጊ ። |
| ፭ኛ ፤ — **አቃበረ** ፡ | (ድርብ)— **አቀባበረ** ፡ | አደራራጊ ። |

ተቀባበረ ፡ ማለት ፣ ድርብነቱ ፣ ለ፫ኛው ፣ ዐምድ ፣ ለተደራጊውም ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ላ፬ኛው ፣ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ይኸውም ፡ ተሰበረ ፣ ተሳበረ ፡ ብሎ ፣ ተሰባበረ ፡ በማለት ፣ ይረዳል ። የ፯ቱ ፣ አ

ዕማድ ፡ ስምና ፡ ግብር ፤ ገቢር ፥ ተገብሮ ፤ ወይም ፡ ማድረግ ፥ መደረግ ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ ይወሰናል ። ፩ኛውና ፡ ፪ኛው ፡ ፭ኛው ፡ ዐምድ ፡ ድርቦቻቸውም ፡ ሳይቀሩ ፡ እነዚኽ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ወገን ፡ ኹነው ፡ በገቢርነት ፡ ይጠራሉ ። ፫ኛውና ፡ ፬ኛው ፡ ከነድርባቸው ፡ እኒኽ ፡ ፪ቱ ፡ ደግሞ ፡ በተገብሮነት ፡ ይጠራሉ ። ዳግመኛም ፡ ተደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ አድራጊነትም ፡ አለውና ፥ ተቃበረ ፡ ማለት ፡ ባንድ ፡ ወገኑ ፡ ከነቀበረ ፡ ይስማማል ። ፮ኛም ፡ ግሱ ፡ እንደ ፡ መጣና ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ያለ ፡ ዐጕል ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፥ ስሙና ፡ ክፍሉ ፡ ከተደራጊነት ፡ ይገባል ። አንቀጻቸውም ፡ ኀላፊና ፡ ትንቢት ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ዐይነት ፡ ይከፈላል ፤ ለ፪ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፪፪ስልት ፡ አላቸው ፤ ፫ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ትእዛዝም ፡ ከትንቢት ፡ ይገባል ።

(ኀላፊ ፡ አንቀጽና ፡ ትንቢት ፡ አንቀጽ)

| (ኀላፊ) | (ያኹንና ፡ ትንቢት) | (ትእዛዝ ፡ አንቀጽ) |
|---|---|---|
| ፩ኛ — **ከፈለ** ፤ | ፪ኛ — **ይከፍል** ። | ፫ኛ — **ይክፈል** ። |
| **ከፍሏል** ፤ (ከፍሎ ፡ አል ፡ ነበር) | **ይከፍላል** ። | |

(ሐተታ) ከፍሏል ፡ ማለት ፡ ዘሩ ፡ ከከፈለና ፡ ከሀሎ ፥ ያውም ፡ ከቦዝ ፡ አንቀጽና ፡ ከኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ የተዴቀለ ፥ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዘንድና ፡ ትእዛዝ ፡ የለውም ። ከፈለ ፡ ግን ፡ መደበኛ ፡ አንቀጽ ፡ ነውና ፥ ኹለቱም ፡ አሉት ፤ ትንቢቱ ፡ ዘንድ ፡ ሲወድቅበት ፡ ማስሪያንቱን ፡ ይለቅና ፡ ርሱ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ይሳባል ። ዘንድ ፡ ከነበ ፡ የወጣ ፡ የውል ፡ ቃልና ፡ የውል ፡ አገባብ ፡ ነው ፤ ፍችውም ፡ እንዲና ፡ ሊ ፡ ናቸው ። ይከፍል ፡ ዘንድ ፡ ሲል ፥ እንዲከፍል ፡ ሊከፍል ፡ ያሰኛል ። በሌላ ፡ አንቀጽም ፡ ሲሳብ ፥ ብድር ፡ ይከፍል ፡ ዘንድ ፡ አይወድም ፤ ወይም ፡ ፈቃዱ ፥ ይከፍል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲገባ ፥ ከሄደ ፡ ዘንድ ፥ ብሎ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ያሰኛል ። በስም ፡ እየገባ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሲል ፥ ቅርብና ፡ አጠገብ ፡ ያሰኛል ። በዘንድ ፡ ፈንታ ፡ ነበርና ፡ ይኾናል ፡ ሲገቡ ፥ ምኞትና ፡ ጠጠት ፡ ጥርጥር ፡ ያሳያል ። ይከፍል ፡ ነበር ፤ ምኞት ። ይከፍል ፡ ይኾናል ፤ ጥርጥር ። ይከፍል ፡ ይኾን ፡ ሲል ፤ ወይም ፡ ብቻውን ፥ ይከፍል ፡ ማለት ፡ ደፍቶ ፡ ሲናገሩት ፥ ጥያቄ ፡ ይኾናል ። በቀረው ፡ ግን ፥ ድር ፡ ቢያብር ፡ አንበሳ ፡ ያስር ፤ ኽርብ ፡ ሲወጉ ፡ ባህያ ፡ ይጠጉ ፤ ሲገዙ ፡ ይገዙ ፤ ሴት ፡ ታውቅ ፡ በወንድ ፡ ያልቅ ፡ እያለ ፡ በየፊቱ ፡ ያስራል ። ፫ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ትእዛዝ ፡ መባሉ ፥ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲነገር ፡ ነው ፤ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ልመናና ፡ ጸሎት ፡ ይባላል ። ከፍሏል ፡ ማለትም ፡ ኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፥ የትንቢቱ ፡ ሥር ፡ ይ ፡ ሲጨመርበት ፥ ተቀባይ ፡ የሌለው ፡ ዐጕል ፡ ትእዛዝ ፡ እየኾነ ፡ ባጓጕል ፡ መንገድ ፡ ይከፍሏል ፡ ያድሏል ፡ ያሰኛል ። ምስጢሩና ፡ ስልቱ ፡ ዐጕል ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ የከፍሏል ፡ ትንቢት ፡ ይባል ፡ ነበር ።

ድርቦች ፡ አዕማድ ፡ ሲገሰሱ ፡ እንደ ፡ መደበኞች ፡ ዘንድና ፡ ትእዛዝ ፡ አላቸው ፤
ትንቢታቸው ፡ ኹሉን ፡ ይደርባል ።

| (ኀላፊ) | (ትንቢት) | (ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| **ከፋፈለ** ፡ | **ይከፋፍል** ፡ | = | = |
| **ከፋፍሏል** ፡ | **ይከፋፍላል** ፡ | | |

ግስ ፡ ኹሉ ፡ በ፱ ፡ መደብ ፡ ሲረባ ፤ ከፈለ ፡ ከፍሏል ፡ ከፍሎ ፡ ነበር ፡ እንዳልነው ፡ ኹሉ ፡ ኹለቱ ፡ ጾታዎች ፡ አይቀሩም ። አኹን ፡ ለጊዜው ፡ ግን ፡ አልና ፡ ነበር ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነበርን ፡ ትተን ፡ አልን ፡ ብቻ ፡ ይዘን ፡ እንሄዳለን ፤ ነበርም ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ ስላለው ፡ ኋላ ፡ ከቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ። ርባታም ፡ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ስሞች ፡ ይጠራል ፤ ደቂቅ ፡ የተባለም ፡ የስምና ፡ የግብር ፡ የነባር ፡ አንቀጽ ፡ ርባታ ፡ ነው ፤ ያውም ፡ ከ፱ ፡ መደብ ፡ አይወጣም ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ አዐና ፡ ሀሐን ፡ በፊቱ ፡ ሲኾኑ ፡ እነሱን ፡ ጕርደ ፡ ራብዕ ፡ ይኾናል ፤

ይኸውም ፡ በትንቢት ፡ መነሻ ፡ በየና ፡ በተ ፡ ይታወቃል ፤ ክፍሏል ፡ ይከፍላልም ፡ ያስረዳል ።

(ዐቢይ ፡ ርባታ)

## ዐዊቅ ፤ ዐዊቆት ፡ (ዖቀ ፡ የዐውቅ ፡ ይዑቅ) ማወቅ ፡ መረዳት ።

| | (ኀላፊ) | (ትንቢትና ፡ ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| (ርሱ) | ዐወቀ ፡ | ያውቅ ፡ | ይወቅ ። |
| (ጽንዕ) | ዐውቋል ፡ | ያውቃል ፡ | |
| (ርሷ) | ዐወቀች ፡ | ታውቅ ፡ | ትወቅ ። |
| | ዐውቃለች ፡ | ታውቃለች ፡ | |
| (አንተ) | ዐወቅኽ ፡ | ታውቅ ፡ | ዕወቅ ። |
| | ዐውቀኻል ፡ | ታውቃለኽ ፡ | |
| (አንች) | ዐወቅሽ ፡ | ታውቂ ፡ | ዕወቂ ። |
| | ዐውቀሻል ፡ | ታውቂያለሽ ፡ | |
| (እኔ) | ዐወቅኹ ፡ ኩ ፡ | ዐውቅ ፡ | ልወቅ ። |
| | ዐውቄያለኹ ፡ | ዐውቃለኹ ፡ | |
| (አንቱ) | ዐወቅኹ ፡ | ታውቁ ፡ | ዕወቁ ። |
| | ዐውቀኹል ፡ | ታውቃለኹ ፡ | |

(ርስዎና ፡ ርሳቸው ። ብዙዎቹም ፡ የሩቅ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች)

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ርሳቸው) | ዐወቁ ፡ | ያውቁ ፡ | ይወቁ ። |
| | ዐውቀዋል ፡ | ያውቃሉ ፡ | |
| (እናንተ) | ዐወቃችኹ ፡ | ታውቁ ፡ | ዕወቁ ። |
| | ዐውቃችኹል ፡ | ታውቃላችኹ ፡ | |
| (እኛ) | ዐወቅነ ፡ | እናውቅ ፡ | እንወቅ ። |
| | ዐውቀናል ፡ | እናውቃለን ፡ | |

እስከዚኽ ፡ መደብ ፡ ይባላል ፤ ከዚኽ ፡ ቀጥሎ ፡ ዝርዝር ፡ ነው ፤ ከጽንዑ ፡ በቀር ፡ ራሱ ፡ ፳፩ ፡ ይኾናል ። የለና ፡ የበ ፡ ዝርዝሮች ፡ ለትና ፡ በትም ፡ እንደ ፡ አልና ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ከዝርዝር ፡ ጋራ ፡ ይዘምታሉ ፤ ለት ፡ የበጎ ፤ በት ፡ የክፉ ፡ ነው ። ይኸም ፤ ዐወቀው ፡ ብሎ ፡ ዐወቀለት ፡ በት ፤ ዐውቆለታል ፡ በታል ። ያውቅለት ፡ በት ፤ ለታል ፡ በታል ፡ እያለ ፡ መሄዱን ፡ ያሳያል ።

(ዝርዝር ፡ ርባታ ፤ ርሱ ፡ የተባለው ፡ ሩቁ ፡ ከርሱ ፡ እስከኛ ፡ ፱ኙን ፡ መደብ ፡ በተራ ፡ ሲያውቃቸው)

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ርሱን) | ዐወቀው(ለት ፡ በት) | ያውቀው ፡ | ይወቀው ። |
| | ዐውቆታል ፡ | ያውቀዋል ፡ | |
| (ርሷን) | ዐወቃት ፡ | ያውቃት ፡ | ይወቃት ። |
| | ዐውቋታል ፡ | ያውቃታል ፡ | |
| (አንተን) (—ችን) | ዐወቀኽ ፤ ሽ ፡ | ያውቅኽ ፤ ሽ ፡ | ይወቅኽ ፤ ሽ ። |
| | ዐውቆኻል ፤ ሻል ፡ | ያውቅኻል ፤ ሻል ፡ | |
| (እኔን) | ዐወቀኝ ፡ | ያውቀኝ ፡ | ይወቀኝ ። |
| | ዐውቆኛል ፡ | ያውቀኛል ፡ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| (አንቱን) | ዐወቀኹ ፤ ዎ ፡ | ያውቅኹ ፤ ዎ ፡ | ይወቅኹ ፤ ዎ ። |
| (ርስዎን) | ዐውቆ኿ል ፤ ዎታል ፡ | ያውቅ኿ል ፤ ዎታል ፡ | |
| (ርሳቸውን) | ዐወቃቸው ፡ | ያውቃቸው ፡ | ይወቃቸው ። |
| | ዐውቋቸዋል ፡ | ያውቃቸዋል ፡ | |
| (እናንተን) | ዐወቃችኹ ፡ | ያውቃችኹ ፡ | ይወቃችኹ ። |
| | ዐውቋች኿ል ፡ | ያውቃች኿ል ፡ | |
| (እኛን) | ዐወቀን ፤ ነ ፡ | ያውቀን ፡ | ይወቀን ፡ |
| | ዐውቆናል ፡ | ያውቀናል ፡ | |

ርሷ ፡ የተባለች ፡ ሩ(ቋ)ቂቱ ፡ ከርሱ ፡
እስከኛ ፡ ፱ኙን ፡ ዘርዝራ ፡ ስታውቅ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቀችው ፡ | ታውቀው ፡ | ትወቀ |
| ዐውቃዋለች ፡ | ታውቀዋለች ፡ | ው ። |
| ዐወቀቻት ፡ | ታውቃት ፡ | ትወቃ |
| ዐውቃታለች ፡ | ታውቃታለች ፡ | ት ። |
| ዐወቀችኽ ፤ ሽ ፡ | ታውቅኽ ፤ ሽ ፡ | ትወቅ |
| ዐውቃኻ(ሻ)ለች ፡ | ታውቅኻ(ሻ)ለች ፡ | ኽ፤ሽ ። |
| ዐወቀችኝ ፡ | ታውቀኝ ፡ | ትወቀ |
| ዐውቃኛለች ፡ | ታውቀኛለች ፡ | ኝ ። |
| ዐወቀችኹ ፤ ዎ ፡ | ታውቅኹ ፤ ዎ ፡ | ትወቅ |
| ዐውቃ኿(ዎታ)ለች ፡ | ታውቅ኿(ዎታ)ለች ፡ | ኹ፤ዎ ። |
| ዐወቀቻቸው ፡ | ታውቃቸው ፡ | ትወቃ |
| ዐውቃቸዋለች ፡ | ታውቃቸዋለች ፡ | ቸው ። |
| ዐወቀቻችኹ ፡ | ታውቃችኹ ፡ | ትወቃ |
| ዐውቃች኿ለች ፡ | ታውቃች኿ለች ፡ | ችኹ ። |
| ዐወቀችን ፡ | ታውቀን ፡ | ትወቀ |
| ዐውቃናለች ፡ | ታውቀናለች ፡ | ን ። |

አንተ ፡ የተባለው ፡ ቅርቡ ፡ ፳ቱን ፡
መደብ ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲያውቅ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኸው ፤ ኻት ፡ | ታውቀው ፤ ቃት ፡ | ዕውቀ |
| ዐውቀኸዋ(ኻታ)ል ፡ | ታውቀዋ(ቃታ)ለኽ ፡ | ው፤ቃት |
| ዐወቅኸኝ ፡ | ታውቀኝ ፡ | ዕወቀ |
| ዐውቀኸኛል ፡ | ታውቀኛለኽ ፡ | ኝ ። |
| ዐወቅኻቸው ፡ | ታውቃቸው ፡ | ዕወቃቸ |
| ዐውቀኻቸዋል ፡ | ታውቃቸዋለኽ ፡ | ው ። |
| ዐወቅኸን ፡ | ታውቀን ፡ | ዕወቀ |
| ዐውቀኸናል ፡ | ታውቀናለኽ ፡ | ን ። |

አንች ፡ የተባለች ፡ ቅር(ቧ)ቢቱ ፡ ፳ቱን ፡
መደቦች ፡ ዘርዝራ ፡ ስታውቅ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅሽው ፤ ሻት ፡ | ታውቂው ፤ ያት ፡ | ዕወቂ |
| ዐውቀሽዋ(ሻታ)ል ፡ | ታውቂዋ(ያታ)ለሽ ፡ | ው፤ያት ፡ |
| ዐወቅሽኝ ፡ | ታውቂኝ ፡ | ዕወቂ |
| ዐውቀሽኛል ፡ | ታውቂኛለሽ ፡ | ኝ ። |
| ዐወቅሻቸው ፡ | ታውቂያቸው ፡ | ዕወቂያ |
| ዐውቀሻቸዋል ፡ | ታውቂያቸዋለሽ ፡ | ቸው ። |
| ዐወቅሽን ፡ | ታውቂን ፡ | ዕወቂ |
| ዐውቀሽናል ፡ | ታውቂናለሽ ፡ | ን ። |

እኔ ፡ ባይ ፡ ፯ቱን ፡ መደብ ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲያውቅ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኹት ፡ | ዐውቀው ፡ | ልወቀ |
| ዐውቄዋለኹ ፡ | ዐውቀዋለኹ ፡ | ው ። |
| ዐወቅ኿ት ፡ | ዐውቃት ፡ | ልወቃ |
| ዐውቄያታለኹ ፡ | ዐውቃታለኹ ፡ | ት ። |
| ዐወቅኹኽ ፤ ሽ ፡ | ዐውቅኽ ፤ ሽ ፡ | ልወቅ |
| ዐውቄኻ(ሻ)ለኹ ፡ | ዐውቅኻ(ሻ)ለኹ ፡ | ኽ፤ሽ ። |
| ዐወቅኹኹ ፤ ዎ ፡ | ዐውቅኹ ፤ ዎ ፡ | ልወቅ |
| ዐውቄ኿(ዎታ)ለኹ ፡ | ዐውቅ኿(ዎታ)ለኹ ፡ | ኹ፤ዎ ፡ |
| ዐወቅ኿ቸው ፡ | ዐውቃቸው ፡ | ልወቃ |
| ዐውቄያቸዋለኹ ፡ | ዐውቃቸዋለኹ ፡ | ቸው ። |
| ዐወቅ኿ችኹ ፡ | ዐውቃችኹ ፡ | ልወቃ |
| ዐውቄያች኿ለኹ ፡ | ዐውቃች኿ለኹ ፡ | ችኹ ። |

አንቱ ፡ የተባሉት ፡ ቅርቡ ፡ ፳ቱን ፡
መደቦች ፡ ዘርዝረው ፡ ሲያውቁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኹ(኿)ት ፡ | ታውቁ(ቋ)ት ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቀኹ(኿)ታል ፡ | ታውቁ(ቋ)ታለኹ ፡ | (ቋ)ት ። |
| ዐወቅኹኝ ፡ | ታውቁኝ ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቀኹኛል ፡ | ታውቁኛለኹ ፡ | ኝ ። |
| ዐወቅ኿ቸው ፡ | ታውቋቸው ፡ | ዕወቋቸ |
| ዐውቀ኿ቸዋል ፡ | ታውቋቸዋለኹ ፡ | ው ። |
| ዐወቅኹን ፡ | ታውቁን ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቀኹናል ፡ | ታውቁናለኹ ፡ | ን ። |

ርስዎና ፡ ርሳቸው ፤ ብዙዎቹም ፡ ወንዶችና ፡ ሴ

ቶች ፡ ሩቶቹ ፤ ፱ኙን ፡ ዘርዝረው ፡ ሲያውቁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቁ(ቋ)ት ፡ | ያውቁ(ቋ)ት ፡ | ይወቁ |
| ዐውቀው(ዋ)ታል ፡ | ያውቁ(ቋ)ታል ፡ | (ቋ)ት ። |
| ዐወቁኽ ፤ ሽ ፡ | ያውቁኽ ፤ ሽ ፡ | ይወቁ |
| ዐውቀውኻ(ሻ)ል ፡ | ያውቁኻ(ሻ)ል ፡ | ኽ፤ሽ ። |
| ዐወቁኝ ፡ | ያውቁኝ ፡ | ይወቁ |
| ዐውቀውኛል ፡ | ያውቁኛል ፡ | ኝ ። |
| ዐወቁኹ ፡ | ያውቁኹ ፡ | ይወቁ |
| ዐውቀውኋል ፡ | ያውቁኋል ፡ | ኹ ። |
| ዐወቋቸው ፡ | ያውቋቸው ፡ | ይወቋቸ |
| ዐውቀዋቸዋል ፡ | ያውቋቸዋል ፡ | ው ። |
| ዐወቋችኹ ፡ | ያውቋችኹ ፡ | ይወቋ |
| ዐውቀዋችኋል ፡ | ያውቋችኋል ፡ | ችኹ ። |
| ዐወቁን ፡ | ያውቁን ፡ | ይወቁ |
| ዐውቀውናል ፡ | ያውቁናል ፡ | ን ። |

እናንት ፡ የተባሉ ፡ ቅርቦቹ ፡ ፰ቱን ፡

መደብ ፡ ዘርዝረው ፡ ሲያውቁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቃችኹ(ኋ)ት ፡ | ታውቁ(ቋ)ት ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቃችኹ(ኋ)ታል | ታውቁ(ቋ)ታላችኹ ፡ | (ቋ)ት ። |
| ዐወቃችኹኝ ፡ | ታውቁኝ ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቃችኹኛል ፡ | ታውቁኛላችኹ ፡ | ኝ ። |
| ዐወቃችኋቸው ፡ | ታውቋቸው ፡ | ዕወቋቸ |
| ዐውቃችኋቸዋል ፡ | ታውቋቸዋላችኹ ፡ | ው ። |
| ዐወቃችኹን ፡ | ታውቁን ፡ | ዕወቁ |
| ዐውቃችኹናል ፡ | ታውቁናላችኹ ፡ | ን ። |

እኛ ፡ ባዮች ፡ ፯ቱን ፡ መደቦች ፡

ዘርዝረው ፡ ሲያውቁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅነው ፡ | እናውቀው ፡ | እንወቀ |
| ዐውቀነዋል ፡ | እናውቀዋለን ፡ | ው ። |
| ዐወቅናት ፡ | እናውቃት ፡ | እንወቃ |
| ዐውቀናታል ፡ | እናውቃታለን ፡ | ት ። |
| ዐወቅንኽ ፤ ሽ ፡ | እናውቅኽ ፤ ሽ ፡ | እንወቅ |
| ዐውቀንኻ(ሻ)ል ፡ | እናውቅኻ(ሻ)ለን ፡ | ኽ፤ሽ ። |
| ዐወቅንኹ ፤ ዎ ፡ | እናውቅኹ ፤ ዎ ፡ | እንወቅ |
| ዐውቀንኋ(ዎታ)ል ፡ | እናውቅኋ(ዎታ)ለን | ኹ፤ዎ ። |
| ዐወቅናቸው ፡ | እናውቃቸው ፡ | እንወቃ |
| ዐውቀናቸዋል ፡ | እናውቃቸዋለን ፡ | ቸው ። |
| ዐወቅናችኹ ፡ | እናውቃችኹ ፡ | እንወቃ |
| ዐውቀናችኋል ፡ | እናውቃችኋለን ፡ | ችኹ ። |

ከ፭ቱ ፡ አዕማድ ፡ ፫ቱ ፡ ድርቦች ፡ ዐዋወቀና ፡ ተዋዋወቀ ፡ አስተዋዋወቀ ፡ ማለት ፡ ከዚኽ ፡ ካወቀ ፡ መደብ ፡ አይገቡም ። የቀሩት ፡ አዕማድ ፡ ግን ፤ አሳወቀና ፡ አስታወቀ ፡ ፩ወገን ፤ ታወቀ ፡ ተዋወቀ ፤ አስተዋወቀ ፤ እንዚኽ ፡ ፬ቱ ፡ በየፊታቸው ፡ ሲረቡ ፡ አርእስትና ፡ ቦዝ ፡ መስምና ፡ ቅጽል ፡ አላቸው ፤ የነገር ፡ ኹሉ ፡ ስምና ፡ ግብር ፡ ጥሬና ፡ ቅጽል ፡ ከማይመስለው ፡ አንቀጽ ፡ አይወጣም ፤ ከሚመስለው ፡ እንጂ ።

| (አርእስት) | (ቦዝ ፡ አንቀጽ) | (መስምና ፡ ቅጽል) |
|---|---|---|
| ፩ኛ ፤ **ማወቅ** ፤ | **ዐውቆ** ፡ | **ዐዋቂ** ፡ ያወቀ ፤ የሚያውቅ ። |
| ፪ኛ ፤ **ማሳ(ስታ)ወቅ** ፤ | **አሳ(ስታ)ውቆ** ፡ | **አሳ(ስታ)ዋቂ** ፤ ያሳወቀ ፡ የሚያስታውቅ ። |
| ፫ኛ ፤ **መታወቅ** ፤ | **ታውቆ** ፡ | **ታዋቂ ፡ ዕውቅ** ፤ የታወቀ ፤ የሚታወቅ ። |
| ፬ኛ ፤ **መተዋወቅ** ፤ | **ተዋውቆ** ፡ | **ተዋዋቂ** ፤ የተዋወቀ ፤ የሚተዋወቅ ። |
| ፭ኛ ፤ **ማስተዋወቅ** ፤ | **አስተዋውቆ** ፡ | **አስተዋዋቂ** ፤ ያስተዋወቀ ፤ የሚያስተዋውቅ ፤ |

**ዕውቂያ ፤ ዕውቀት** ፡ ከማወቅና ፡ ከመታወቅ ፡ ከመተዋወቅ ፡ ይወጣሉ ፤ ስምነታቸውም ፡ የሥራና ፡ ያሠራር ፡ ስም ፡ ነው ። ሲዘረዝርም ፡ ዕውቂያው ፡ ዋ ፤ ዕውቀቱ ፡ ቷ ፤ ዕውቂያኽ ፤ ሽ ፤ ዕውቀትኽ ፡ ሽ ፤ ዕውቂያዬ ፡ ዕውቀቴ ፡ እያለ ፡ ፱ኙን ፡ መደቦች ፡ ይጠቅሳል ፤ ይኸውም ፡ ደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ይባላል ። ባዕድ ፡ አብዢ ፡ ወይም ፡ ማብዣ ፡ ዎች ፡ ነው ፤ ዕውቂያዎች ፡ ዕውቀቶች ፤ ዐዋቆች ፡ ዐዋቂዎች ። ቶች ፡ ቆች ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ውጣና ፡ ጕርደ ፡ ነው ። ዐዋቂ ፡ ያወቀ ፡ ከኀላፊ ፤ የሚያውቅ ፡ ከትንቢት ፡ ይወጣል ፤ የቀሩትም ፡ ያራቱ ፡ አዕማድ ፡ ቅጽሎች ፡ አወጣጣቸ

ው ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ፣ ባንዱ ፡ የኹሉ ፡ ይታወቃል ። በዝ ፡ አንቀጽ ፡ ደግሞ ፡ አልና ፡ ነበር ፡ ሲስቡት ፤ ወይም ፡ ሲዘምቱበት ፡ ኀላፊነቱ ፡ በ፱ ፡ ጽንዕ ፡ ይፈታል ፣ ጽንዕ ፡ ማለትም ፡ ጥናት ፡ ጥ ኑነት ፡ ጥንካሬ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባላፊ ፡ ጊዜና ፡ ባላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ዐይነት ፡ ክፍል ፡ አለ ፣ ዐወቀ ፣ ያኹን ፡ የቅርብ ፤ የዛሬ ፡ የትላንት ፤ ጥቂት ፡ የቈየ ። ዐውቋል ፣ የዋለ ፡ ያደረ ፤ የሰነበተ ፡ የዘገየ ። ዐውቆ ፡ ነበር ፣ ፈጽሞ ፡ ያለፈ ፡ የኖረ ፤ ወይም ፡ ያረጀ ፡ የቀረ ። የትንቢቱም ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ እን ደ ፡ ኀላፊው ፡ ነው ፣ ይኸውም ፡ ይከፍል ፣ ይከፍላል ፣ ይከፍል ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ባንቀጹ ፡ ሦስ ትነት ፡ ይታወቃል ። ርባታው ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ አል ፡ ባሉታ ፡ ሞክሼነት ፡ ይቀርና ፤ ነበር ፡ ብቻ ፡ በኹሉ ፡ ይዘምታል ፣ በዘንድም ፡ ፈንታ ፡ እንዲና ፡ ሊ ፡ በራብዕነት ፡ ይገባሉ ። አሉታው ም ፡ አል ፡ ም ፡ ነው ፣ አል ፡ አለ ፡ በቃል ፡ ኹሉ ፡ ሥር ፡ በመነሻ ፣ ም ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ መድረሻ ፡ እየኾነ ፡ ይገባል ። (ማስረጃ)

ኢዐዊቅ ፣ (ኢያቀ ፤ ኢየዐውቅ ፣ ኢይዐውቅ) አለማወቅ ።

| (ኀላፊ) | (ትንቢት) | (ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| አላወቀም ፡ (ነበር) | አያውቅም ፡ (ነበር) | እንዳ(ላ)ያውቅ ፡ | አይወቅ ። |

(ቅጽልና ፡ ስም)

አላዋቂ ፤ ያላወቀ ፣ የማያውቅ ።

(በዝ ፡ አንቀጽ)

(ኢዐዊቆ ፣ ቃ) ሳያውቅ ፣ ሳታውቅ ።

ግስን ፡ ኹሉ ፡ እንዲኽ ፡ እያልኽ ፡ አርባ ፨

---

ክፍል ፡ ፫ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ ታሪክም ፣ ይኸውም ፡ በባላገር ፡ የሚኖሩ ፡ አባትና ፡ እ ናት ፡ ሕፃናት ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ፡ በኋላ ፡ የሚያስተምሯቸው ፡ ነው ።

(ተረት ፡ ተረት ፤ የላም ፡ በረት) ።

(አ)—እውነት ።

እውነትና ፡ ዕብለት ፡ ውሃና ፡ እሳት ፡ እነዚኽ ፡ አራቱ ፡ ዐብረው ፡ ዘመ ቱና ፡ ያገኙትን ፡ ኹሉ ፡ ማርከው ፡ ዘርፈው ፡ ይዘው ፡ ሲመለሱ ፤ መቼም ፡ አቶ ፡ ዕብለት ፡ ለተንኰል ፡ አያርፍምና ፣ ወደ ፡ ውሃ ፡ ቀርቦ ፡ አንተ ፡ እሳ ትን ፡ ግደለውና ፡ (አጥፋውና) ፣ ያገኘነውን ፡ ኹሉ ፡ ለሦስት ፡ እንካፈላለ ን ፡ ብሎ ፡ መከረው ። ሞኙ ፡ ውሃም ፡ ወደ ፡ ወሰዱት ፡ የሚሄድ ፡ ስለ ፡ ኾ ነ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ እሳትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢረጫጠው ፡ ሞተ ፡ (ጠፋ) ። ከዚኽም ፡ በኋላ ፡ አካሄዱን ፡ አይተኽ ፡ ጭብጦዉን ፡ ቀማው ፡ እንዲሉ ፣ ወደውነት ፡ ቀርቦ ፤ እውነት ፡ ከብታችንን ፡ ይዘን ፡ ወደ ፡ ዳገት ፡ አለው ። ውሃም ፡ አሻቅቦ ፡ መውጣት ፡ አይኾንለትምና ፣ ራሱን ፡ ይዞ ፡ እ የጮኸ ፡ ቊልቊል ፡ ሄደ ፡ (ወረደ) ። እውነትና ፡ ዕብለትም ፡ ከብቱን ፡ ኹ ሉ ፡ ነድተው ፡ ወዳገር ፡ ቤት ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አቶ ፡ ዕብለ ት ፡ እውነትን ፡ ከድቶ ፡ ከብቱ ፡ ኹሉ ፡ የኔ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አሽከ